# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
# የ2014 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ ሪፖርት

## ለኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበ

**ነሐሴ 2013**
**አዲስ አበባ**

# ማ ው ጫ


| | | |
|---|---|---|
| 1. | መ ግ ቢ ያ ........................................ | 1 |
| 2. | አጠቃላይ ተቋማዊ ሁኔታ........................................ | 1 |
| 3 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ባጭሩ........................................ | 3 |
| 4. | በ2013 በጀት ዓመት የባንኩ የስትራቴጂካዊ መስኮች ዕቅድ አፈፃፀም ባጭሩ........................................ | 7 |
| 5. | ማጠቃለያ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች........................................ | 12 |
| 6 | የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ........................................ | 13 |
| 7. | ማ ጠ ቃ ለ ያ ........................................ | 15 |
| | አባሪ ሠንጠረዥ........................................ | 16 - 33 |

# 1. መ ግ ቢ ያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የአሥር ዓመት ዕቅድ እና የሦስት ዓመት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም እንዲሁም ፣ የባንኩን ራዕይ፣ ተልዕኮና ኃላፊነት፣ ያለፈውን ዓመት የዕቅድ ክንውንና ባንኩ ያለውንና ሊኖረው የሚገባውን የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሀብት ያገናዘበ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡ ዕቅዱም በ5 ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች በ23 ስትራቴጂካዊ ግቦችና በ4 እይታዎች የተዋቀረ የውጤት ተኮር የሥራ አፈፃፀም ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

በዝግጅት ምዕራፍ ባንኩ የ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ከመገምገሙም ባሻገር የ2014 ዕቅድ በአመራሩና በሠራተኛው ሙሉ ተሳትፎ አዘጋጅቷል፡፡ ዕቅዱንም ከሥራ ሂደት እስከ ግለሰብ ፈፃሚዎች ድረስ አውርዷል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ የዕቅዱን አፈፃፀም በቋሚነት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት የዘረጋ ሲሆን፣ አስፈላጊው የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግብአት በወቅቱ የሚቀርብበትን ስልት ነድፎ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

# 2. አጠቃላይ ተቋማዊ ሁኔታ

## 2.1 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ስትራቴጂካዊ ግቦች

**የባንኩ ራዕይ**

- ከአፍሪካ ጠንካራና ስመ-ጥር ማዕከላዊ ባንኮች አንዱ መሆን፡፡

**ተልዕኮ**

- «የተረጋጋ ዋጋና የውጭ ምንዛሬ ተመን እንዲኖር ማድረግ፣ አስተማማኝ የፋይናንስ ሥርዓት እንዲሰፍን ማበረታታትና ለፈጣን እና ቀጣይ የኢኮኖሚ ልማት አስተዋጽኦ ማበርከት» ፡፡

**ዋና እሴቶች**

- ተጠያቂነት፣
- ግልፅነት፣
- ጥሩ የቡድን ሥራ መንፈስ፣
- ምስጢር መጠበቅ፣

- ቀጣይነት ያለው መሻሻል፣
- የፋይናንስ ዲስ□ሊን፣ እና
- መልካም የሆነ የሙያተኝነት ተግባር ማሳየት፡፡

## 2.2 የብሔራዊ ባንክ ዋና ዋና ሥራዎችና አገልግሎቶች

- ፖሊሲ ነክ ጥናቶችን ማካሄድና መንግሥትን የማማከር አገልግሎት መስጠት፣
- የባንክ፣ የክፍያና የሂሳብ ማወራረድ አገልግሎት መስጠት፣
- የገንዘብ ኖቶችና ቅንስናሽ ገንዘቦችን ማሳተም፣ ማሠራጨትና ከጥቅም ውጭ የሆኑትን ማስወገድ፣
- ተፈላጊ የኢኮኖሚና የፋይናንስ መረጃዎችን ማዘጋጀትና ማቅረብ፣
- የውጭ ምንዛሪ ማስተዳደር፣
- መመሪያዎችና ደንቦችን ማውጣት፣
- ለፋይናንስ ተቋማት የሥራ ፈቃድ መስጠትና ማደስ፣
- የፋይናንስ ተቋማትን መቆጣጠርና ሪፖርት ማቅረብ፣
- የገንዘብና የፋይናንስ ዘርፍ እንቅስቃሴ ሪፖርቶችና ሕትመቶችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፣
- የፋይናንስ መረጋጋት ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡

## 2.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች

1. የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ፣
2. የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ማድረግ፣
3. ከፍተኛና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ፣
4. የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት ማስፈን፣
5. የአሠራር ልህቀት ማምጣት፡፡

## 2.4 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስትራቴጂካዊ ግቦች

1. የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ፣
2. የተረጋጋ የውጭ ምንዛሬ ተመን እንዲኖር ማድረግ፣
3. ቀጣይነት፣ ሰፊ መሠረት ያለውና አካታች የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት፣
4. የተረጋጋና ደህንነቱ የተጠበቀ የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል፣
5. የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል፣
6. የባንኩን ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል፣

7. የፋይናንስ አካታችነትና የፋይናንስ ደንበኞችን ደህንነት ማሳደግ፣
8. የሞኒተሪ ፖሊሲ አስተዳደርን ማሻሻል፣
9. የገንዘብ እና የውጭ ምንዛሪ ገበያ ልማትን የበለጠ ማሻሻል፣
10. በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እንዲኖር ማድረግ፣
11. የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ፣
12. በቂ የብድርና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ፣
13. የፖሊሲ አማካሪነት ድርሻን ማረጋገጥና ወደፊትን ያማከለ የፖሊሲ ትንተናን ማጠናከር፣
14. የፋይናንስ ተቋማት አስተዳደርንና ቁጥጥር ማጠናከር፣
15. የክፍያ ሥርዓትን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ውጤታማነት የበለጠ ማሻሻል፣
16. የከረንሲ አስተደደር ሥርዓትን ማሻሻል፣
17. የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል፣
18. የፋይናንስ ዘርፉን የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ማሻሻል፣
19. የ□ሮጀክት አስተዳደርንና የትግበራ ውጤታማነትን ማሻሻል፣
20. የባንኩን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስታንዳርድ የበለጠ ማሻሻል፣
21. የባንኩን ሠራተኞች የቴክኒክ ብቃት፣ የአመራር ችሎታና የሥራ ባህል ማሻሻል፣
22. የባንኩን የአስተደደር፣ የሪስክና የቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር፣ እና
23. የባንኩን ስታንዳርድ፣ የሥርዓተ ፆታና የወጣቶች፣ እንዲሁም የሥነ-ምግባር ሥራዎች ትግበራ ውጤታማነት ማሻሻል፡፡

# 3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ባጭሩ

ባንኩ ለ2013 በጀት ዓመት ያዘጋጃቸውን ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮችና ግቦች መሠረት በማድረግ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን  የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና ወደ ነጠላ አሃዝ ለማቅረብ፣ የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን የተረጋጋ እንዲሆን ለማድረግ፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትና የመጠባበቂያ ክምችት አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ለቁጠባና ኢንቨስትመንት መስፋፋት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣ ከፍተኛና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ለመደገፍ፣ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ ሆኖ እንዲቀጥልና የሚጠበቅበትን የፋይናንስ አገልግሎት ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን እንዲሰጥ ለማድረግ፣ እንዲሁም የባንኩን የአሠራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ  የሚያስችሉ ተግባራትን ለመፈፀም ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል፡፡  በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተከናወኑት በርካታ ሥራዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1 በባንኩ ውስጥ የውጤት ተኮር፣ የመልካም አስተዳደርና የአሠራር ውጤታማነትና ቅልጥፍና ማሻሻልን በተመለከተ

### 3.1.1 ውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት

- ባንኩ ውጤት ተኮር ምዘና የአሠራር ሥርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል ከባንኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ በተመነዘሩ እና በበጀት ዓመቱ ሊሠሩ በታቀዱ ሥራዎች ላይ ውጤታቸውን በዒላማ እና በሥራ ውጤት በመከፋፈል፣ እንዲሁም ቁልፍ የሥራ ጠቋሚዎችን መነሻ በማድረግ በየደረጃው ከሚገኙ ኃላፊዎች ጋር በመፈራረም ወደ ሥራ ተገብቶ ሥራዎች በዚሁ አግባብ ተከናውነዋል፡፡
- የሠራተኞች የሥራ የአፈፃፀም ምዘና በየስድስት ወሩ ተከናውኖ፣ በተገኘው ውጤት ላይ በአመራር ደረጃ ውይይት ተደርጎበት የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲደረጉ አቅጣጫ ተሰጥቶበታል፡፡ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓቱንም ለማሻሻል የሚረዳ የ360 ድግሪ የምዘና አሠራር ትግበራ ክትትል ተደርጎ የትንተና ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሁሉም የሥራ ክፍሎች እንዲያውቁት ተልኳል፡፡

### 3.1.2 የለውጥ አመራርና መልካም አስተዳደርን በተመለከተ

- በየደረጃው ባለው አመራር እንዲሁም በአመራርና በፈፃሚዎች ደረጃ በየጊዜው ስብሰባዎችን በማካሄድ፣ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ፣ የሥራ ክንውን ክትትልና ግምገማ በማድረግ፣ ያጋጠሙ ችግሮችን አቅም በፈቀደ መጠን በመፍታትና በተነሡ ጉዳዮች ላይ በወቅቱ ግብረ መልስ በመስጠት በዕቅድ የተያዙ ተግባራት እንዲፈፀሙ ጥረት ተደርጓል፡፡

- በባንኩ ውስጥ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት እንዲቻል በየሥራ ክፍሉ የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫዎች በሠራተኛው ሙሉ ተሳትፎ ተለይተው በባንክ ደረጃ በሰነድነት ከማጠናቀር ባለፈ፤ የተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የአሠራር ሂደቶች እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሻሻሉ በመደረጉ የኪራይ ሰብሳቢነትን አመለካከት ከሥር መሠረቱ ለማስወገድ የሚያስችሉ በጎ ጅምሮች ታይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተቀናጀ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ በሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠ አገራዊ ማሳሰቢያ መሠረት፣ በባንኩ ውስጥ ሀብታቸውን ማስመዝገብና ማሳደስ የሚገባቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲያስመዘግቡና እንዲያሳድሱ ተደርጓል፡፡

- የባንኩን የሥነ ምግባር ደረጃ ለማሻሻል በወጣው ዕቅድ መሠረት በየጊዜው የሥነ ምግባር የአፈፃፀም ክትትል ተደርጓል፡፡ ለሠራተኞች ስለ ሥነ-ምግባር የግንዛቤ ማስጨበጫ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሁለት ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሌላ የየሩብ ዓመቱ የሥነ-ምግባር የአፈፃፀም ሪፖርት ለፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተልኳል፡፡ በግንባርም ሆነ አስተያየት መስጫ ሣጥኖችንና የባንኩን ዌብሳይት በመጠቀም ከጠቋሚዎች የደረሱ ጉዳዮችን በመመርመር ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ምላሽም እንዲሰጥ ሆኗል፡፡

- ከአቅርቦት አኳያ በዝግጅት ምዕራፍ የተነደፈውን ዕቅድ መነሻ በማድረግ በትግበራ ምዕራፍ ለባንኩ ሥራ መሳካት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የመሣሪያዎች እንዲሁም የክህሎትና የቴክኖሎጂ አገልግሎቶች እንዲሟሉ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከሰው ኃይል ልማት አኳያ እጥረት ቢኖርም ክፍት የሥራ መደቦች በተቻለ መጠን በቅጥርና በዝውውር ተሞልተዋል፡፡ የባንኩን ሠራተኞች ክህሎት ለማሳደግ በወጣው ዕቅድ መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተዘጋጁ የተለያዩ የአቅም ግንባታና የሥልጠና ፕሮግራሞች ላይ ሠልጣኞች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

### 3.1.3 <u>የሕዝብ ክንፍ በተመለከተ</u>

- ከውጭ ደንበኞች ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ክፍሎች ዓመታዊ የባለድርሻ አካላት የመወያያ የጊዜ ሠሌዳቸውን ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ የኮቪድ-19 ጫና ቢኖርም ከባንኩ ደንበኞችና ባለድርሻ አካላት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ስብሰባዎችና የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው በመልካም አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥና እንዲሁም በመመሪያዎች ዙሪያ በሚታዩ ችግሮች ላይ ግልፅ ውይይት ተደርጎ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

- የባንኩን ወቅታዊ ሪፖርቶችና መረጃዎች ለተገልጋዮች በወቅቱ የማቅረብ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ ከዓለም ባንክ እና ከንግድ ባንኮች እንዲሁም ከተለያዩ ደንበኞች ለተነሡ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ንግድ ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ሊዝ ኩባንያዎች በዜጎች ቻርተር ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

- የአገሪቱን የክፍያ ሥርዓት ዘመናዊና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ ከማድረግ አኳያ የተጀመረው የኢትዮጵያ ኦቶሜትድ ትራንስፈር ሥርዓትና ባንኮች ስለ ተበዳሪዎች መረጃ የሚለዋወጡበት የመረጃ ማዕከል የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

- አዲስ የገንዘብ ኖቶችን ከማሳተምና የገንዘብ ለውጥ ከማድረግ ባሻገር የባንኩን የገንዘብ አቅርቦትና ስርጭት ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ወርቅ አቅራቢዎች ሳይጉላሉ ወርቅ የሚያቀርቡበትና ክፍያ የሚያገኙበት የተሻሻለ አሠራር ተዘርግቷል፡፡

### 3.1.4 <u>ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን በተመለከተ</u>

- የባንኩ የ2013 በጀት ዓመት የ6 ወር የሰብዓዊ መብት አፈፃፀም ሪፖርት ለፌዴራል አቃቤ ሕግ ተልኳል፡፡

- በባንኩ ውስጥ የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ከወሊድ ጋር በተገናኘ የሚደርስባቸውን እንግልት ለመቀነስ የሕፃናት ማቆያ ለመገንባት ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡ በተያያዘ ለባንኩ ሴት ሠራተኞች የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

- የሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤን ለማሳደግ ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀንን /March 8/ አስመልክቶ በባንኩ ለሚገኙ ሴት አመራሮች በአመራር ብቃት ዙሪያ የአራት ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የነጭ ሪቫንና የHIV ቀንን በተለያዩ የማነቃቂያ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ-ግብሮች ለማክበር በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ በኮቪድ-19 ምክንያት ሳይከናወን ቀርቷል፡፡ ነገር ግን ይህን ክፍተት ለመሙላትና የባንኩን ሠራተኞች ግንዛቤ ለማሳደግ ፖስተሮችንና የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለሁሉም የሥራ ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- በሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ እንቅስቃሴ ባንኩ ሠራተኞችን በማስተባበር ከ9 ሺህ በላይ ችግኞችን ተክሎ በመንከባከብ ላይ ይገኛል፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ደግሞ የብር ሁለት መቶ ሺህ ዋጋ ያላቸው ችግኞችን በመግዛት ለልደታ ክፍለ ከተማ አስረክቧል።

- **"ደም በመለገስ ህይወትን እናድን"** እና **"ደማችን ለሠራዊታችን"** የሚሉ አገራዊ ጥሪዎችን መነሻ በማድረግ የባንኩ ማኔጅመንት እና ሠራተኞች ደም እንዲለግሡ ተደርጓል፡፡

- በብር ለውጥ ሂደት ከፍተኛ ተሳትፎ ላበረከቱ የውጭና የውስጥ ባለድርሻ አካላት የምስጋናና የዕውቅና ሠርተፊኬት ተበርክቷል፡፡

## 4 በ2013 በጀት ዓመት የባንኩ የስትራቴጂካዊ መስኮች ዕቅድ አፈፃፀም ባጭሩ

### 4.1 የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ

- የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲሰፍን ከማድረግ አኳያ፣ ባንኩ በ2013 በጀት ዓመት የዋጋ ንረትን ለመቀነስና በነጠላ አሃዝ ለመገደብ የወጣውን የረጅም ጊዜ ዕቅድ በተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል፡፡ ይህንንም ለማሳካት ባንኩ መሠረታዊ የገንዘብ መጠን ከዋጋ ንረት ጋር የተጣጣመ እንዲሆንና የወለድ ተመን የአገሪቱን የቁጠባና የኢንቨስትመንት ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ እንዲመራ ጥረት አድርጓል፡፡ ከዚህ ሌላ መንግሥት በቀጥታ ብድር መልክ ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደው የገንዘብ መጠን በዕቅዱ መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ አከናውኗል፡፡ በየሁለት ሣምንቱ የግምጃ ቤት ሰነድ ጨረታ በማካሄድ ለመንግሥት አማራጭ የበጀት ጉድለት መሸፈኛ የሚሆን የገንዘብ ሀብት ከማሰባሰብ ባሻገር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት በገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያነት ተጠቅሞበታል፡፡

- ይህ ሁሉ ሆኖ የዋጋ ንረት በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነጠላ አሃዝ በላይ 24.5 በመቶ ደርሷል፡፡ ይህም የሆነው በዋናነት የምርት አቅርቦት ከፍላጎት ጋር ባለመመጣጠኑ፣ እንዲሁም በዓለም ገበያ የሸቀጦች ዋጋ የማንሠራራት አዝማሚያ በማሳየቱና ከመጋቢት ወር 2012 ጀምሮ  የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ  ተፅዕኖ ባለመርገቡ ነው፡፡

### 4.2 የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ማረጋጋትና የውጭ ክፍያ ሚዛን ማሻሻል

- ባንኩ የብር የውጭ ምንዛሪ ተመንን ለማረጋጋት ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል፡፡ በዚሁ መሠረት የብር ዋጋ ከዋና ዋና ዓለም አቀፍ ገንዘቦች አኳያ አላስፈላጊ መዋዠቅ እንዳይታይበት በዕለታዊ የባንክ ለባንክ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን በበጀት ዓመቱ 12.1 ሚሊዮን ዶላር ለባንኮች ሸጧል፡፡  እንዲሁም ከውጭ ለሚገቡ ነዳጅ፣ መሠረተ ልማት ግንባታና ማስፋፊያ የሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎችን ለመሳሰሉ መሠረታዊ ሸቀጦች ግዥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ 4.5 ቢሊዮን ዶላር ያህል የውጭ ምንዛሪ አቅርቧል፡፡

- የሀገሪቱን የወጭ ንግድ ተወዳዳሪነት ለማጠናከር ሲባል በባንኮች የብር ዋጋ ከአሜሪካን ዶላር አኳያ በቀጣይነት እንዲቀንስ በመደረጉ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የብር ዋጋ በአማካይ በ24.5 በመቶ ቀንሷል፡፡

- ከዚህ ሌላ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካላት የንግድ ልውውጥና የኢኮኖሚ ግንኙነት አኳያ አስተማማኝና በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እንዲኖራት ባንኩ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር አድርጓል፡፡ የወጪና የገቢ ንግድ፣ የሐዋላና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰትን የሚያሳዩ ወርሃዊና ሩብ ዓመታዊ መረጃዎች ተሰብስበውና ተተንትነው ለፖሊሲ ግብአትነት ውለዋል፡፡

- በዚህም መሠረት በ2013 በጀት ዓመት ከሸቀጦች ወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ 3.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የደረሰ ሲሆን፣ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት 21.1 በመቶ ጨምሯል፡፡ በተመሳሳይ ለሸቀጦች ገቢ ንግድ የተደረገው ወጪ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት በ2.9 በመቶ አድጎ 14.3 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል፡፡ በመሆኑም የአገሪቱ የንግድ ሚዛን ጉድለት ከአምናው መጠነኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡

- በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ ከግል ሐዋላ (ከግለሰቦችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች) የተሰበሰበው የተጣራ ገቢ 6.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል፤ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ22.3 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ከግለሰቦች ሐዋላ የተገኘው ገቢ በ20.7 በመቶ እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተገኘው ገቢ በ27.9 መቶ ከፍ በማለቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከተጣራ የመንግሥታዊ የውጭ ሐዋላ የተገኘው 1.4 ቢሊዮን ዶላር ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ11.1 በመቶ ቀንሷል፡፡

- በአንፃሩ የተጣራ የማዕከላዊ መንግሥት የረጅም ጊዜ ብድር በ65.8 በመቶ እና የግል ድርጅቶች የረጅም ጊዜ የተጣራ ብድር በ6.6 በመቶ ሲቀንስ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የረጅም ጊዜ የተጣራ ብድር ጉድለት ከ720.9 ሚሊዮን ዶላር ወደ 848.7 ሚሊዮን ዶላር አሻቅቧል፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የአጭር ጊዜ ካፒታል እንቅስቃሴ ከ149.4 ሚሊዮን ዶላር ጉድለት ወደ 259.3 ሚሊዮን ዶላር ጉድለት ሰፍቷል፡፡ በሌላ በኩል የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 64.1 በመቶ ዕድገት በማሳየት 4 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል፡፡ በመሆኑም የተጣራ የካፒታል ሂሳብ ሚዛን 9.6 በመቶ ቅናሽ አስመዝግቧል፡፡

- የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማጠናከርና የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ በተወሰዱ እርምጃዎች የተነሣ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት በሰኔ ወር 2013 መጨረሻ ለ2.2 ወር የገቢ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ወጪ ለመሸፈን ወደሚያስችል ደረጃ ደርሷል፡፡ ይህም ከዕቅዱ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 4.3 የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት ማስፈን

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነትና ዕድገት ለማረጋገጥ በወሰዳቸው የቁጥጥርና የክትትል እርምጃዎች የፋይናንስ ዘርፉ ጉልህ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ የባንክ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች ብዛት የ17.8 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት 7,349 ደርሷል፡፡ የፋይናንስ ተደራሽነትና የድርጅቶቹ ትርፋማነትም እንዲሁ ጨምሯል፡፡

- ባንኮች በበጀት ዓመቱ ያሰባሰቡት ተቀማጭ ሂሳብ ከአምናው 30.54 በመቶ ዕድገት በማሳየት ብር 1.36 ትሪልዮን ደርሷል፤ የባንክ ደብተር ያላቸው ሰዎች ቁጥር በ36.47 በመቶ ጨምሮ 71.59 ሚሊዮን ሆኗል፡፡ እንዲሁም ባንኮች የሰጡት አዲስ ብድር (ቦንድን ጨምሮ) ብር 1.3 ትሪልዮን የደረሰ ሲሆን፣ ይህም ካለፈው ዓመት 21.3 በመቶ ይበልጣል፡፡ ጠቅላላ የብድር ክምችት (ቦንድን ጨምሮ) 21.7 በመቶ በማሻቀብ ወደ ብር 1.4 ትሪልዮን ከፍ ብሏል፡፡ የተሰበሰበው ብር 154.3 ቢሊዮን ሲሆን፣ 6.5 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አሳይቷል፡፡ የክፍያው ሁኔታ አጠራጣሪ የሆነ ብድር መጠን 3.5 በመቶ ሲሆን፤ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 5 በመቶ ጣሪያ በታች መሆኑ አበረታች ውጤት ነው፡፡

- የኢትዮጵያ ልማት ባንክን በተመለከተ፣ ባንኩ በበጀት ዓመቱ የሰጠው አዲስ ብድር ከአምናው በ15.9 በመቶ አድጎ ብር 9.9 ቢሊዮን፣ የሰበሰበው ብድር ደግሞ በ19.9 በመቶ ጨምሮ ብር 9.2 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ የባንኩ የማይመለስና አጠራጣሪ ብድር ከአጠቃላይ ብድር ሲሰላ ከ33.6 በመቶ ወደ 20.2 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አሃዝ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 15 በመቶ ጣሪያ ከፍ ያለ መሆኑ ባንኩ የፋይናንስ አቋሙን ለማሻሻል አሁንም በበለጠ ትጋትና ጥንቃቄ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

- የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በበጀት ዓመቱ ለሕይወት፣ ለኃላፊነት እና ለንብረት የሰጡት የመድን ሽፋን ብር 5.66 ትሪልዮን፣ የቅርንጫፎቻቸው ብዛት ደግሞ 5 በመቶ አድጎ 635 ደርሷል፡፡ የኢንሹራንስ ዘርፉ የሀብት ዕዳን የመክፈል አቅም በብሔራዊ ባንክ ከተደነገገው 100 በመቶ ወለል በላይ 295 በመቶ ሆኗል፡፡

- አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትም 4.7 ሚሊዮን የብድር ደንበኞችን በማፍራት የቁጠባ፣ የብድርና ተዛማጅ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቁጥር 42 የደረሰ ሲሆን፣ የቅርንጫፎች እና ንዑስ ቅርንጫፎች ብዛት ደግሞ 2,189 ደርሷል፡፡ ከእነዚህ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት መካከል ስምንቱ የሞባይል እና ኤጀንት

ባንኪንግ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ፣ ሰኔ ወር 2013 መጨረሻ በ21,270 ወኪሎቻቸው (ኤጀንቶች) አማካይነት ከ2.8 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ አካውንቶችን በማስከፈት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

- እስከ ሰኔ 2013 መጨረሻ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ያሰባሰቡት ቁጠባ ብር 52.40 ቢሊዮን፣ በደንበኞች እጅ ያለ ጠቅላላ ብድር ብር 69.64 ቢሊዮን፣ ጠቅላላ ሀብት ብር 104.96 ቢሊዮን እና ካፒታል ብር 27.88 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የቁጠባ መጠን 17.2 በመቶ፣ በደንበኞች እጅ ያለ ጠቅላላ ብድር 6.7 በመቶ፣ ካፒታል 43.4 በመቶ እንዲሁም ጠቅላላ ሀብት 13.8 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ የብድር ደንበኞች ቁጥር ግን በኮቪድ-19 ተፅዕኖ ምክንያት ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረበት 5.3 ሚሊዮን ወደ 4.7 ሚሊዮን ዝቅ ብሏል፡፡ በሌላ በኩል በእነዚህ ተቋማት የሚንቀሳቀሰው የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር የ3.2 በመቶ ዕድገት በማሳየት 22.3 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ የተጣራ ትርፋቸው ደግሞ ብር 3.03 ቢሊዮን ሆኗል፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ፣ ስድስት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያዎች ለ4,925 ተገልጋዮች የብር 1.55 ቢሊዮን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አቅርበዋል፡፡ የኩባንያዎቹ ጠቅላላ ሀብት ብር 4.56 ቢሊዮን፣ ካፒታላቸው ደግሞ ብር 2.30 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ጠቅላላ ሀብት 16.8 በመቶ ማደጉን ያሳያል፡፡

- ከዚህ ሌላ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት በመላ አገሪቱ እንዲሰፍን ተደርጓል፤ በዚህም ሁሉም ባንኮች ዋና መ/ቤቶች፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና የማዕከላዊ የካርድ ስዊች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚያስተዳድረው የክፍያ ሥርዓት ጋር በመተሳሰራቸው ለሁሉም ተሣታፊ አካላት ወጥና ቀልጣፋ የእርስ በርስ የክፍያ፣ ሂሳብ የማጣራትና የማወራረድ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት የመጠበቅና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጥ የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎችን አጠናክሮ እየሠራ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የክፍያ ሥርዓቱን ቅልጥፍናና ተደራሽነት ለማሻሻል በክፍያ ሥርዓቱ ተሳታፊ የሆኑ ባንኮች ሁሉ የኮር ባንኪንግ ሥርዓት የዘረጉ ሲሆን፣ የካርድ ነክ ተያያዥ የክፍያ መፈፀሚያ መሣሪያዎችን ተደራሽነትና ዓይነት ለመጨመር የሚያስችል ብሔራዊ ማዕከላዊ ስዊች ተቋቁሞ በባንኮች በኩል በተለያዩ የክፍያ መንገዶች የሚፈፀሙ ክፍያዎችን እንዲናበቡ በማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡

- ባንኩ በቂ የገንዘብ አቅርቦት መኖሩን ከማረጋገጥ ባሻገር ለአዲስ የገንዘብ ለውጥ የሚያስፈልጉ የብር ኖቶችን የማሳተምና ወደ አገር ውስጥ የማስገባትና የማሠራጨት ሥራ በዕቅዱ መሠረት አከናውኗል፡፡ የአሮጌ የገንዘብ ኖቶችን የመሰብሰብ፣ የመምረጥና የመቁጠር እንዲሁም አገልግሎት የማይሰጡትን የማስወገድ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 4.4 ከድጋፍ ሥራዎች አንፃር የተከናወኑ ሌሎች ተግባራት

- በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ የባንኩ ጠቅላላ የሰው ኃይል 1,059 የደረሰ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 1,047 ቋሚ፣ ቀሪዎቹ 12 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 75 ክፍት የሥራ መደቦች በቅጥርና በዕድገት፣ በተጠባባቂነት በዝውውር የተሞሉ ሲሆን፣ 26 ሠራተኞች በልዩ ልዩ ምክንያት ከባንኩ ተሰናብተዋል፡፡ 235 ሠራተኞች በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ወስደዋል፡፡ እንደዚሁም በኢትዮጵያ የፋይናንስ ጥናት ተቋም አማካይነት በ2013 3,495 ሠራተኞች ከተለያዩ የአገሪቱ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በተለያዩ የአመራርና የቴክኒክ ሙያ የአጭር ጊዜ ኮርሶች ላይ ሥልጠና ወስደዋል፡፡

- የኢንፎርሜሽንና የኮሙኒኬሽን ሥርዓት አስተዳደርን ቅልጥፍናና ውጤታማነት ለማሻሻልም ባንኩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት የማሻሻል ሥራ ሠርቷል፡፡ ከኢንፎርሜሽን ሥርዓት ደህንነት አኳያም ስጋቶችን በመለየት በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ መስተካከል ያለባቸውን በማስቀመጥ ለተግባራዊነቱ ተንቀሳቅሷል፡፡

## 4.5 የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል

- የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር በተመለከተ ባንኩ በ2013 በጀት ዓመት ብር 18.2 ቢሊዮን ጠቅላላ ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ ከንውኑ ብር 14.1 ቢሊዮን በመሆኑ ከዕቅዱ 22.4 በመቶ ያንሳል፡፡ በአንፃሩ የባንኩ የሥራ ማስኬጃ (መደበኛ) ወጪ ብር 8.3 ቢሊዮን እንደሚደርስ ታቅዶ፣ አፈፃፀሙ ብር 14.95 ቢሊዮን ወይም ከዕቅዱ 19 በመቶ ይበልጣል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ የካፒታል ወጪ ብር 1.86 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዶ ከአንዳንድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምና ከቋሚ ዕቃዎች ግዥ ሂደት መስተጓጎል ጋር በተያያዘ ክፍያዎች በመዘግየታቸው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ወጪው ብር 52.3 ሚሊዮን ሆኗል፡፡

- በጥቅሉ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተጣራ ገቢ (በጠቅላላ ገቢና በመደበኛ ወጪ መካከል ያለው ልዩነት) ብር 0.21 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም ከዕቅዱ 103.7 በመቶ ያንሳል፡፡

# 5 ማ ጠ ቃ ለ ያ

## ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

- በበጀት ዓመቱ ውስጥ ባንኩ ካጋጠሙት ዐበይት ተግዳሮቶች መካከል የዋጋ ንረት የማሻቀብ አዝማሚያ ማሳየት፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል አለመሟላትና ዝቅተኛ የፕሮጀክት አፈፃፀም ናቸው፡፡

- ባንኩ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በወሰዳቸው የፖሊሲ እርምጃዎች፡-

  ሀ/ በነጠላ አሃዝም ባይሆን የዋጋ ንረትን በ24.5 በመቶ ለመገደብ ተችሎአል፡፡

  ለ/ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ያስከተለውን ችግር ለማቃለል የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የሚያጠናክሩ እርምጃዎችን ከመውሰድ ባሻገር የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች የሚቀርብበትን ሁኔታና የባንኮች የውጭ ምንዛሪ ድልድል ግልጽነትን የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

  ሐ/ የፕሮጀክት አፈፃፀምን ለማጠናከር የቅርብ ክትትል የተደረገ ቢሆንም፣ በአቅም ማነስና በተለያዩ ምክንያቶች ችግሩን በተፈለገው መጠን ማቃለል አልተቻለም፡፡ ለወደፊቱ ችግሩን ለመቅረፍ የተጠናከሩ የማሻሻያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

  መ/ በኮቪድ ምክንያት የተፈለገውን ያህል ባይሆንም አዲስ ሠራተኞችን የመቅጠርና ነባሮቹን የማሳደግ፣ ለሠራተኞች የሙያና የክህሎት ማዳበሪያ ሥልጠናዎችን የመስጠትና የጥቅማ ጥቅም ማሻሻያዎችን የማድረግ እርምጃዎች በመወሰዳቸው የባንኩን የሰው ኃይል ችግርና ፍልሰት በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

- በጥቅሉ ባንኩ ከላይ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት አቅም በፈቀደ መጠን ተግቶ የተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ አዎንታዊ ውጤቶችም ተመዝግበዋል፡፡ ከዚህ ሌላ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይፈፀሙ የቀሩ ሥራዎችንና ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጎ ተፈፃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተቀናጀ ጥረት ይደረጋል፡፡

# 6. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ

- የባንኩን ተልዕኮና ራዕይ እንዲሁም የሀገሪቱን የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እንዲሁም የሦስት ዓመት የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ □ሮግራም መሠረት በማድረግ፣ የ2013 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት አፈፃፀም በመገምገምና የፊዚካልና የፋይናንስ አቅምን በማገናዘብ እንዲሁም ሌሎች የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የ2014 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

- የዕቅዱ ዋና ዋና የትኩረት መስኮች በአራት እይታዎች (የተገልጋይ እይታ፣ የፋይናንስ እይታ፣ የውስጥ አሠራር እይታ፣ የመማማርና ዕድገት እይታ) እና በ23 ስትራቴጂካዊ ግቦች ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ ተግባራቱም በዝግጅት፣ በተግባርና በማጠቃለያ ምዕራፍ በሚከናወኑበት አግባብ ተቃኝተዋል፡፡

- በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት በዕቅዱ ላይ በየደረጃው ውይይት የተደረገበት ሲሆን፣ የፀደቀው ዕቅድም ወደ ፈፃሚ ደረጃ ተመንዝሮ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ለበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገው የአቅርቦትና የሠራተኛ ክህሎት ሁኔታም ተመቻችቷል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ ዕቅዱ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ሀብትን፣ የዕቅዱን ታሳቢዎች እንዲሁም የክትትል፣ የድጋፍና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የዕቅዱ ዝርዝር በየሩብ ዓመት ተዘጋጅቶ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## 6.1 ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

| ተ.ቁ. | ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች | ውጤት |
|---|---|---|
| 1. | የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ | ባለአንድ አሃዝ የዋጋ ንረት |
| 2. | የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ማድረግ | ከሚዛናዊ የምንዛሪ ተመን ጋር የተጣጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመን |
| 3. | የኢኮኖሚ ዕድገት | ከፍተኛና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት |
| 4. | የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት ማስፈን | ደህንነቱ የተጠበቀ የፋይናንስ ሥርዓት |
| 5. | የአሠራር ልህቀት ማምጣት | የተገልጋዮች እርካታና አመኔታ |

## 6.2 የዕቅዱ ታሳቢዎች

የባንኩ የ2014 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ ሲዘጋጅ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ታሳቢ ተደርገዋል፡-

- የሀገሪቱ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድና የሦስት ዓመት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድ፣
- ባንኩ በ2013 በጀት ዓመት ያከናወናቸው ተግባራትና በ2014 በጀት ዓመት ለማከናወን የሚፈልጋቸው ፕሮግራሞች፣
- የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት ቀጣይነት፣
- የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅርቦት፣
- የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ሥርዓት መሻሻል ቀጣይነት፣
- ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች፡፡

## 6.3 የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት ፍላጎት

### 6.3.1 የሰው ኃይል ፍላጎት

በ2013 በጀት ዓመት የባንኩ ቋሚ የሰው ኃይል 1,059 የነበረ ሲሆን፣ በ2014 ወደ 1,275 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

### 6.3.2 የበጀት ፍላጎት

በ2014 በጀት ዓመት ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች ብር 16.2 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በአንፃሩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለሚተገበሩ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ለሚሆን መደበኛ ወጪ ብር 11.3 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪዎች ደግሞ ብር 2.34 ቢሊዮን ተመድቧል፡፡ የባንኩ የተጣራ ገቢም ብር 4.6 ቢሊዮን እንደሚሆን ዕቅድ ተይዟል፡፡

## 6.4 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

- የባንኩ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የተዘጋጀው በሠራተኛውና በአመራሩ ሙሉ ተሳትፎ ሲሆን፣ በተለያዩ የሥራ ሂደቶች፣ በባንኩ ከፍተኛ ሥራ አመራር፣ በሲኒየር ማነጅመንት እንዲሁም በባንኩ ቦርድ ደረጃ ሰፊና ግልጽ ውይይት ተደርጎበት የፀደቀ ነው፡፡

- ከዚህ ሌላ፣ ሊሠሩ የታቀዱ ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በቡድን፣ በሥራ ሂደቶች፣ በኤክስኩቲቭ ማነጅመንት፣ በሲኒየር ማነጅመንትና በተቋም ደረጃ የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡ ግብረ መልስም በወቅቱ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ወቅታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የተለያዩ አካላት ይቀርባሉ፡፡

## 7. ማ ጠ ቃ ለ ያ

ለማጠቃለል ያህል፣ ባንኩ ከአሥር ዓመቱ የስትራቴጂክ ዕቅድና ከሦስት ዓመቱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ □ሮግራም የተመነዘሩና በባንኩ ስትራቴጂካዊ ግቦች ውስጥ የተመለከቱ ተግባራትን ለማከናወን ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን፣ ለበጀት ዓመቱ የተቀመጡትን ስትራቴጂካዊ ግቦች ለማሳካት በቁርጠኝነት ወደ ትግበራ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ በዕቅዱ የተካተቱ ዝርዝር ተግባራት በቀጣዩ በአባሪ ተመልክተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የ2014 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| 1. ተገልጋዮች | 1 | የዋጋ መረጋጋትን ማስፈን | የብር የመግዛት ኃይል የተረጋጋ እንዲሆን ማድረግ | ከዋጋ ንረት ግብ ጋር የተጣጣመ የሪዘርቭ ገንዘብ ዕድገት ሪፖርት | ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | የሀገር ውስጥ ብድር ከግቡ ያለው ልዩነት | ›› | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአገር ውስጥ የዋጋ ንረት ትንተና ረቂቅ ሪፖርት /ትንበያን የያዘ/ ማዘጋጀት | ›› | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | 2 | ከፍተኛና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት | ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች በቂ የብድር አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ | ወርሃዊ የንግድ ባንክ የብድር አቅርቦት | ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | 3 | በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን ማስፈን | | እውነተኛው የውጭ ምንዛሪ ተመን ከግቡ ያለው ልዩነት መጥበብ | ህጋዊው የውጭ ምንዛሪ ተመን ከግቡ ያለው ልዩነት መጥበብ | ≤5% | ≤5% | ≤5% | ≤5% | ≤5% | |
| | | | ትንበያን የያዘ የውጭ ምንዛሪ ሪፖርት ማዘጋጀት | ሣምንታዊ የውጭ ምንዛሪ ገበያ መከታተያ ሪፖርት ማዘጋጀት | ሪፖርት | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | |
| | 4 | የተረጋጋ፣ ጤናማና አካታች የፋይናንስ ሥርዓት ማስፈን | የተረጋጋ፣ ጤናማና ተደራሽ የፋይናንስ ዘርፍ | ስቴቢሊቲ ሪፖርት | የደንበኞች እርካታ መጨመር በመቶኛ | 74/69%[1] | - | - | - | 74/69% | |
| | | | | | የካፒታል ብቃት ጥምርታ | ቢያንስ 8% ለባንኮች | ቢያንስ 8% ለባንኮች | ቢያንስ 8% ለባንኮች | ቢያንስ 8% ለባንኮች | ቢያንስ 8% ለባንኮች | |
| | | | | | | ≥20% ለኢንሹራንስ | ≥20% ለኢንሹራንስ | ≥20% ለኢንሹራንስ | ≥20% ለኢንሹራንስ | ≥20% ለኢንሹራንስ | |
| | | | | | | ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | ቢያንስ 12% | ቢያንስ 12% | ቢያንስ 12% | ቢያንስ 12% | |

[1] ለውጭ ደንበኞች እርካታ 74% ሲሆን፣ ለውስጥ ደንበኞች 69% ለዓመቱ የተቀመጠ ግብ ነው፡፡

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | | | ለሊዝ ፋይናንስ ቢያንስ 10% | ቢያንስ 10% | ቢያንስ 10% | ቢያንስ 10% | ቢያንስ 10% | |
| | | | | | አጠራጣሪና የተበላሸ ብድር | ቢበዛ 5% (ለባንኮች ለአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት እና ለሊዝ ፋይናንስ) | ቢበዛ 5% | ቢበዛ 5% | ቢበዛ 5% | ቢበዛ 5% | |
| 2. ፋይናንስ | 2.1 | | የባንኩን የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻል | ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት | በጊዜ የተዘጋጀ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 3. የውስጥ አሠራር | 3.1 | | የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ | ወርሃዊ የመንግሥት ቦንድ ቁጠባ ሪፖርት | በወቅቱና በጥራት የቀረበ ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት መያዝ | ሣምንታዊ የኢ.ብ.ባ. የውጭ ምንዛሪ ፍሰት ትንተና ሪፖርት | የቀረበ ሪፖርት ጥራትና ብዛት | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | |
| | | | | የውጭ ምንዛሪ ክምችት መጠን በወር ገቢ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ወጪ መሸፈን | በወር የገቢ መሸፈኛ | 2.2 | 2.2 | 2.2 | 2.2 | 2.2 | |
| | | | | ሩብ ዓመታዊ የውጭ ንግድ ሁኔታና ትንተና | የቀረበ ሪፖርት ጥራትና ብዛት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | ደህንነቱ የተረጋገጠ የውጭ ምንዛሪ ክምችት | በመመሪያው መሠረት የተፈፀመ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የኢ.ብ.ባ. መመሪያዎችን ማስፈፀም | በመመሪያው መሠረት የተፈፀመ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የተጠናቀቀ የወጪና ገቢ ንግድ | 2 መመሪያዎች | 2 | - | 1 | - | 1 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.2 | የገንዘብ አስተዳደር (Monetary Management) ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል | | የመንግሥት ብድር መጠን ሪፖርት | ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | የተቀማጭ ሂሳብ መጠን የሚገልጽ ሪፖርት | » | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | ለመንግሥት ቦንዶች ሁለተኛ ገበያ ማቋቋም | የቀረበ ሰነድ | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | ወርሃዊ የግምጃ ቤት ሠነድ ሽያጭ | ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | 3.3 | የፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ውጤታማነት ማጠናከር | የባንክ ዘርፍ ቁጥጥር ውጤታማነት ማጠናከር | የተዘጋጁ/አዲስ የተከለሱ መመሪያዎች ማውጣት | ተዘጋጅተው የተረቀቁ/የወጡ መመሪያዎች ብዛት | 5 | 1 | 1 | 1 | 2 | |
| | | | | የተዘጋጀ የባንክ ዘርፍ ጤንነትና የእያንዳንዱ ባንክ የተናጠል ምዘና ሪፖርት | የምዘና ሪፖርት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | በየሩብ ዓመቱ የተዘጋጀ የተቀማጭና ብድር ሥርጭት ሪፖርት | የሪፖርት ብዛት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | የተዘጋጀ ወርሃዊ የሀብት፣ የብድር፣ የተቀማጭና የካፒታል ዕድገት ሪፖርት | የተዘጋጀ ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | የተዘጋጁ የክትትል ምርመራ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ሪፖርቶች | 7 | 1 | 2 | 1 | 3 | |
| | | | | የአደጋ ተጋላጭነትን መሠረት ያደረጉ በቦታው በመገኘት የተደረጉ የቁጥጥር ሪፖርቶች | የሪፖርት ብዛት | 7 | - | 4 | 1 | 2 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | ወቅታዊና የተጠናከረ ተቋማዊ መረጃ (Institutional Profile) ማዘጋጀት | ወቅታዊና የተጠናከረ ተቋማዊ መረጃ (Institutional Profile) | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የተዘጋጀ ሣምንታዊ የባንኮች ገንዘብ አከል ሀብት ሪፖርት | አፈፃፀም በመቶኛ | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | |
| | | | | የተዘጋጀ የ2014 የባንኮች የቁጥጥር ዕቅድ | የተዘጋጀ ዕቅድ ሰነድ | 1 | 1 | - | - | - | |
| | | | | የተዘጋጀ የባንክ ዘርፍ አማካይ የዋስትና ብድር ሽፋን ሪፖርት | የተዘጋጀ ሪፖርት ብዛት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | የባንክ ሱፐርቪዥን አገልግሎት ማቀላጠፍ | ለባንኮችና ለባንክ ቅርንጫፎች አዲስ ፈቃድ መስጠት/ማደስ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | አዳዲስ የባንክ አገልግሎቶች ፈቃድ መስጠት | ›› | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የባንክ ኃላፊዎችን ሹመት እንዲሁም የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤና የዳይሬክተሮች ቦርድ ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | ከባንኮች ማህበርና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ | የተደረጉ ውይይቶች ብዛት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | ወቅታዊ ባንክ ነክ መረጃዎችንና ድጋፎችን መስጠት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | 3.4 | | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን ማጠናከር | በ9 ኢንሹራንሶች ላይ በቦታው ተገኝቶ የተደረገ የመልስ ምርመራ ሪፖርት | የምርመራ ሪፖርት | 9 | - | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | 4 በቦታው ሳይገኙ የተደረገ የምርመራ ሪፖርቶች | በቦታው ሳይገኙ የምርመራ ሪፖርት በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | 3 የተለያዩ መመሪያዎችን ማውጣት | የሚወጡ መመሪያዎች | 3 | - | - | 1 | 2 | |
| | | | | 3 የተለያዩ መመሪያዎችን ማዘጋጀት | የሚዘጋጁ መመሪያዎች በቁጥር | 3 | - | - | 1 | 2 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን ዕቅድ ማውጣት | የወጣ ዕቅድ | 1 | 1 | - | - | - | |
| | | | | የእያንዳንዱ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወቅታዊ የተቋም መግለጫ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን አገልግሎት ማሳደግ | ለኢንሹራንሶች አዲስ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ የመመሥረቻና የመተዳደሪያ ጽሑፎችንና ቃለጉባኤዎችን፣ እንዲሁም የኢንሹራንስ ዳይሬክተሮችን፣ ዋና እና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎችን ሹመት እና የኢንሹራንስ ፖሊሲዎችን ማፅደቅ | በዜነች ቻርተር መሠረት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የሩብ ፣ የግማሽ፣የዘጠኝ ወራትና ዓመታዊ ሪፖርት ማዘጋጀትና መረጃዎችን መስጠት | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | ከደንበኞች ጋር የሚደረግ ስብሰባ | በቁጥር | 2 | - | - | 1 | 1 | |
| | 3.5 | | የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እና የካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ ቁጥጥር ሥራን ማጠናከር | የተለያዩ ረቂቅ መመሪያዎችን ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ረቂቅ መመሪያዎች | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | 2ኛ ዙር የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት የብድር መረጃ ወደ ብድር መረጃ ቋት የሚካተትበትን □ሮጀክት መተግበር | አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት የብድር መረጃ ቋት ማስፋፊያ □ሮጀክት ማጠናቀቅ | 100% | 95% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | ዳይሬክቶሬቱ ከአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚያደርገው የoff-site መረጃ ልውውጥ በዘመናዊ ሲስተም የተደገፈ መድረግ | ዘመናዊ የon-line (BSA) መረጃ ልውውጥ ትግበራ እንዲጠናቀቅ ማድረግ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | በዓለም አቀፍ አማካሪዎች እገዛ አ/ፋ ተቋማት የሚመሩበት የ “crisis Management” ማዘጋጀት | አ/ፋ ተቋማት የሚመሩበት የ “crisis Management” Framework ማዘጋጀት | 100% | 25% | 50% | 85% | 100% | |
| | | | | ከIFC አማካሪዎችጋር በመሆን የሊዝ ፋይናንስ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ላይ መሥራት | የድርጊት መርሀ-ግብርን መሠረት ያደረገ ውጤታማ የፕሮጀክት ትግበራ መፈጸም | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የ2014 የቁጥጥር ዕቅድ (supervisory plan) ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የቁጥጥር ዕቅድ | የቁጥጥር ዕቅድ ሰነድ | 1 | - | - | - | |
| | | | | በየሩብ ዓመቱ ከመስክ ውጪ የሚዘጋጁ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ዘርፍ ሪፖርት | ከመስክ ውጪ የተዘጋጁ ጥራታቸውንና ጊዜያቸውን የጠበቁ ሪፖርቶች | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | በየሩብ ዓመቱ ከመስክ ውጪ የሚዘጋጁ የሊዝ ፋይናንስ ዘርፍ ሪፖርት | ከመስክ ውጪ የተዘጋጁ ጥራታቸውንና ጊዜያቸውን የጠበቁ ሪፖርቶች | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | በተቋማት ላይ የሚወሰዱ የቁጥጥር እና የእርምት እርምጃዎችን ማጠናከር | በወቅቱ የተወሰደ እርምጃ | 1 ሳምንት | 1 ሳምንት | 1 ሳምንት | 1 ሳምንት | 1 ሳምንት | |
| | | | | የተቋማቱን የውጭ ኦዲተር ሹመት የማፅደቅ፣ | የፀደቀ የተቋማቱ የውጭ ኦዲተር | 1 የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | 1 የሥራ ቀን | |
| | | | | በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ላይ የመስክ ምርመራ ማካሄድ | የ መስክ ምርመራ ሪፖርት | 13 | 4 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላይ የመስክ ክትትል ምርመራ ማካሄድ | የመስክ ምርመራ ሪፖርት | 10 | 2 | 2 | 3 | 3 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | የሊዝ ፋይናንስ ላይ የክትትል ምርመራ ማካሄድ | የክትትል ምርመራ ሪፖርት | 2 | - | - | 1 | 1 | |
| | | | | ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በወቅቱ ማቅረብ | በወቅቱ የተዘጋጁ ሪፖርቶች | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | ወቅታዊና የተጠናከረ ተቋማዊ መረጃ (Institutional Profile) | ጥራቱንና ጊዜውን ጠብቆ የተዘጋጀ ተቋማዊ መረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም "CAMEL" ሪፖርት ማዘጋጀት | የተናጥል ትንተና "CAMEL" ሪፖርት ለሁሉም ማዘጋጀት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የማይክሮፋይናንስ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ዉጤታማነትን ማሻሻል | አዲስ ለሚቋቋሙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያዎች የተሰጠ የሥራ ፈቃድ መስጠት | በዜጎች ቻርተር መሠረት | 60 ቀናት | 60 ቀናት | 60 ቀናት | 60 ቀናት | 60 ቀናት | |
| | | | | የአነስተኛ ፋይናንስ እና ሊዝ ኩባንያ ኃላፊዎች ሹመት | በጊዜው የተሰጠ/የፀደቀ ሹመት በዜጎች ቻርተር መሠረት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | |
| | | | | የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት/ሊዝ ኩባንያ ኃላፊዎችን ሹመት እንዲፀድቅ ማድረግ | የተሰጠ /የፀደቀ የሥራ አስፈፃሚዎች፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት በዜጎች ቻርተር መሠረት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | በ15 የሥራ ቀናት | |
| | | | | አዳዲስ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎችን ማፅደቅ | በዜጎች ቻርተር መሠረት | በ30 ቀን ውስጥ ማጠናቀቅ | 30 ቀን | 30 ቀን | 30 ቀን | 30 ቀን | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.6 | | የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ማሻሻል | የክፍያ ሥርዓቱን የተመለከቱ የስታትስቲክስ መረጃዎችን ማጠናቀርና ሪፖርት ማቅረብ | በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጅ ሪፖርት በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | በክፍያ ሥርዓት ኦፐሬተሮችና ክፍያ መፈጸሚያ መሣሪያ አውጪዎች ላይ ክትትልና የመስክ ምርመራ ማድረግ | የክትትል ሪፖርት በቁጥር | 2 | - | 1 | - | 1 | |
| | | | | የክፍያ ሥርዓት ተሣታፊዎችን የኮር ባንኪንግ እና ተመሣሣይ ሲስተሞች ተናባቢነት ላይ ፍተሻ ማድረግና ማረጋገጫ መስጠት | የሚቀርብ ጥያቄን ማስተናገድ እና ሪፖርት ማዘጋጀት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | በዕቅዱ መሠረት ሣምንታዊ የግምጃ ቤት ሰነዶች ጨረታ ተከናውነዋል | የተዘጋጀ ሠነድ | 36 | 9 | 9 | 9 | 9 | |
| | | | | የኢትዮጵያ አውቶሜትድ ትራንስፈር ሲስተምን የአገልግሎት ዋጋ ፖሊሲ ሠነድን ማዘጋጀትና በሥራ ላይ ማዋል | የተዘጋጀ ሠነድ | 1 | - | 1 | - | - | |
| | | | | ለኢኤቲኤስ ተሣታፊዎች የሚሆን የሊኩዲቲ አስተዳደር የሥራ መመሪያ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ መመሪያ | 1 | 1 | - | - | - | |
| | | የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ማሻሻል | የሥራ ሂደቱን አገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና ማሻሻል | ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶችን ማድረግ | የተከናወኑ ውይይቶች በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | ለክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተሮች የሥራ ፈቃድ መስጠት እና ማደስ | በተለጠጠ መለኪያ የተሰጠ አገልግሎት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የክፍያ ሥርዓት ኦፐሬተሮችና የክፍያ መፈጸሚያ መሣሪያ አውጪዎችን የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔዎችን መመርመርና ማጽደቅ | በተለጠጠ መለኪያ የተሰጠ አገልግሎት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ | | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም | የዓመቱ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |

| | | ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | | መለኪያ | ዒላማ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.7 | ከረንሲ ማኔጅመንት ዘመናዊ ማድረግ | የገንዘብ ስርጭት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ኢሹ ቅርንጫፍ በመላክ ስምምነት ላይ መድረስ | የተዘጋጀ የገንዘብ ሥርጭት | የተዘጋጀ ዕቅድ | 1 | - | - | 1 | - | |
| | | | በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ስርጭት ለኢሹ ቅርንጫፎችና ለግል ባንኮች ማካሄድ | የተሠራጨ ገንዘብ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | አሮጌ ገንዘብ የመምረጥ፣ የመቁጠር፣ የማዘጋጀትና የማስወገድ ሥራ ማከናወን | የተመረጠና የተወገደ አሮጌ ገንዘብ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | ገንዘብ ማሳተም፣ሳንቲሞችን አስቀርጾ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት | ታትሞ/ተቀርጾ ወደ አገር ውስጥ የገባ ገንዘብ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | በኢሹ ቅርንጫፎች ላይ ምርመራ ማካሄድ | የተደረገ ምርመራ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የባንኮችን የኢሹ ሂሳብ ማስታረቅ ሥራን ማከናወን | የታረቀ ሂሳብ | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | ንግድ ባንኮች የሚመሩበት የጥሬ ገንዘብ ዝውውር የአሠራር እና የፖሊሲ ሠነድ አዘጋጅቶ ማቅረብ | ተጠንቶ የቀረበ ጥናት | ተጠንቶ የቀረበ ጥናት | 1 | - | - | 1 | - | |
| | | | ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ማዘጋጀት | የተዘጋጅ መመሪያዎች | ተዘጋጅተው የቀረቡ መመሪያዎች | 5 | 2 | 2 | 1 | - | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.8 | | የፋይናንስ አካታችነትን ማሳደግ | የዲጂታል ፋይናንስን የማስፋፋት ሥራ ላይ ማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | የዲጂታል አካዉንት ቁጥር በ100 ጎልማሶች | 40 | 28.75 | 32.5 | 36.25 | 40 | |
| | | | | አገልግሎቱ በበቂ ባልተዳረሰባቸው ክልሎች የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | አገልግሎት በበቂ ባልተዳረሰባቸው ክልሎች መደበኛ የትራንዛክሽን ሂሳብ ቁጥር መጨመር | እንደ የክልሉ ሁኔታ የሚወሰን | እንደ የክልሉ ሁኔታ የሚወሰን | እንደ የክልሉ ሁኔታ የሚወሰን | እንደ የክልሉ ሁኔታ የሚወሰን | እንደ የክልሉ ሁኔታ የሚወሰን | |
| | | | | የሴቶች የፋይናንስ አካታችነትን ለማሳደግ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | የሴቶች መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ለ100 ሴቶች | 55 | 50.5 | 52 | 53.5 | 55 | |
| | | | | ቁጠባን የማሳደግ ሥራ ላይ ማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ለ100 ጎልማሶች | 143 | 136.25 | 138.5 | 140.75 | 143 | |
| | | | | ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ተደራሽነት ላይ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለየግሉ ሴክተር ከተሰጠ ብድር ያላቸው ድርሻ በመቶኛ | 6% | 5.25% | 5.50% | 5.75% | 6% | |
| | | | | ጠንካራ አነሰተኛ የመድን ሥርዓት መዘርጋት ላይ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | አነስተኛ የመድን ፖሊሲ ቁጥር | አልተለየም | አልተለየም | አልተለየም | አልተለየም | አልተለየም | |
| | | | | ሸሪአ መርህን የተከተለ የፋይናንስ ምርቶችና አገልግሎቶችን የማሳደግ ሥራ ላይ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | የሸሪአ መርህን የተከተለ ሂሳብ በ 100 ሙስሊም ጎልማሶች | 6 | 5.25 | 5.5 | 5.75 | 6 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | የፋይናንስ ደንበኞች ጥበቃ ሥራ ላይ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ሪፖርት | በመመሪያው መሠረት በፋይናንስ ተቋማትና በብሔራዊ ባንክ የተፈቱ ቅሬታዎች በመቶኛ | 90% | 90% | 90% | 90% | 90% | |
| | | | | የፋይናንስ ትምህርት ሥራ ላይ የማስተባበር፣ ክትትልና ግምገማ ርፖረት | በተለያዩ ሁኔታዎች የፋይናንስ ትምህርትን የተከታተሉ ጎልማሶች ቁጥር | 2 | 0.5 | 1.0 | 1.5 | 2.0 | |
| | | | | ለብድር ዋስትና የሚቀርቡ የተንቀሳቃሽ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ላይ የማስተባበር፣ የመከታተልና የማስፈጸም ሪፖርት | ኢትዮጵያ አሁን ያላትን ለቢዝነስ ሥራ ምቹነት ደረጃን ማስቀጠል/ማሻሻል | 8/12 | 8/12 | 8/12 | 8/12 | 8/12 | |
| | | | | የፋይናንስ አካታቸነት መረጃ አሰባሰብና ትንተናን ማጠናከር | የመረጃ አሰባሰብና ትንተናን ማጠናከር | | 1 | | | | |
| | | | የፋይናንስ አካታችነት ጽ/ቤትን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትንና ብቃትን ማሳደግ | ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶችን ማዘጋጀት | መደበኛ ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክና ለፓርላማ | 8 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | | | | ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | ዓመታዊ በጀት ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ዓመታዊ በጀት | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | መረጃና የምክር አገልግሎት መስጠት | የደንበኞች እርካታ | 74% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.9 | የባንኩን የዕቅድና በጀት ዝግጅት እና የአፈፃፀም ሪፖርት ማሻሻል | የባንኩን የዕቅድና በጀት ዝግጅት እና የአፈፃፀም ሪፖርት ማሻሻል | የባንኩን የቀጣይ 5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የዕቅድ ሠነድ | 1 | - | 1 | - | 1 | |
| | | | | የተዘጋጀ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ | የዕቅድ ሠነድ | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | የተዘጋጀ ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድና በጀት | የበጀት ሠነድ | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | የተዘጋጁ ሩብ ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች | ሩብ ዓመታዊ ሪፖርቶች | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | የተዘጋጀ የአፈፃፀም ክትትል ሪፖርት | የተዘጋጀ የአፈፃፀም ክትትል ሪፖርት | 8 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | 3.10 | | የሰው ኃይል አገልግሎት ማሻሻል | በቅጥር /ዕድገት/ ዝውውር የሚሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች | ክፍት የሥራ መደቦችን መሙላት | 738 | 369 | 26 | 299 | 44 | |
| | | | | በጊዜ እና በጥራት የተደረጉ ክፍያዎችና የተሰጡ የፐርሶኔል አገልግሎቶች | የተሰጡ አገልግሎቶች ብዛት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የተዘጋጀ የ2014 የስልጠና ዝርዝር ዕቅድ | በጊዜ እና በጥራት የተመዘነ የዕቅድ ሰነድ | 1 | 1 | -- | -- | -- | |
| | | | | ወርሃዊ የባንኩ ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ ሪፖርት | ወርሃዊ ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | በኢትዮጵያ የፋይናንስ ጥናት ተቋም የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማጠናከር | በሥልጠና የተሳተፉ የኢብባና የባንኮች፣የኢንሹራንስ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ሠልጣኞች ብዛት 4,525 | ብዛት በመቶኛ | 100% | 15% | 25% | 35% | 25% | |
| | | | | የትራንስፖርትና የኢንጅነሪንግ አገልግሎት ጥራትና ፍጥነት መጨመር | ለባንኩ ሕይወትና ንብረት አስተማማኝ የደህንነትና የፀጥታ አገልግሎት መስጠት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | በቴክኖሎጂ የታገዘ የሴኩሪቲ ሥራ ማከናወን | ➢የአጠቃቀም ብቃት<br>➢የአፈፃፀም ሪፖርት<br>➢የሚሠራ መሣሪያ መሆኑን ማረጋገጥ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.11 | የግዢ አገልግሎት | የባንኩን የግዢ አገልግሎት ጥራት ማሻሻል | የሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት | በጥራት እና ጊዜ የተለካ ሪፖርት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | ወርሃዊ የሂሳቦች ማወራረጃ ሪፖርት | በጥራት እና ጊዜ የተለካ ሪፖርት | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | ዓመታዊ የግዢ ዕቅድ | በጥራት እና ጊዜ የተለካ ዕቅድ | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | ግዢዎችን መፈፀም | ከዕቅዱ አንፃር የተከናወነ ግዢ | 90% | 15% | 60% | 15% | - | |
| | 3.12 | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ማነጅመንት ልምድን ውጤታማነት ማሻሻል | ፖሊሲና መመሪያ መከለስ | የተከለሰ መመሪያ | በፐርሰንት/አጠቃቀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ዕውቀት ማዳበር | የሠለጠኑና በሥልጠና የተለወጡ ሠራተኞች ብዛት | ብዛት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | አይቲ ሱፐርቪዥን በንግድ ባንኮች ማከናወን | ሱፐርቫይዝ የተደረጉ ባንኮች ብዛት | በፐርሰንት/አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የባንኩን የኔትወርክ ኢንፍራስትራክቸርና ሲስተም ማሻሻል እና ፕሮጀክት መከታተል | የተሻሻለ ኢንፍራስትራክቸር፣ ኔትወርክ ሲስተም እና የተፈፀሙ ፕሮጀክቶች | በፐርሰንት/አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | ኢንፎርሜሽን ማሰራጨትና ተደራሽነትን ማስፋት | የተተገበረ ዘመናዊ መረጃ ሥርዓት | በፐርሰንት/አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የተጠቃሚን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ የሰፖርትና የጥገና አገልግሎት መስጠት | የሲስተምና ኢንፍራስትራክቸር ሰፖርትና ጥገና ድጋፍ በጊዜ መስጠት | በፐርሰንት/አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | የባንኩን ኢንፎርሜሽን ሲስተም ደህንነት አጠባበቅ ማጠናከር | ደህንነቱ የተጠበቀ ኢንፎርሜሽን ሲስተም | በፐርሰንት/አፈፃፀም በመቶኛ | 99% | 99% | 99% | 99% | 99% | |
| | | | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ተደራሽነትን ማስፋትና ዘመናዊ ማድረግ | በባንኩ ውስጥ የተተገበረ ዘመናዊ መረጃ ሲስተም | የአይቲ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ደረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | | የአይቲ ስታንዳርድ መተግበር | 70% | | | | 70% | |
| | | | | | ሲስተም ተደራሽነት | 97% | 97% | 97% | 97% | 97% | |
| | 3.13 | | ከለውጥና መልካም አስተዳደር ትግበራ አንፃር የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሻሻል | የዜጎች ቻርተር ሰነድን ትግበራ መከታተል | የተደረገ ክትትል | አፈጻጸም በመቶኛ | 100% | - | - | 100% | |
| | | | | ከባንኩ ባለድርሻ አካላትጋር የሚደረግ የውይይት የጊዜ ሠሌዳ ዕቅድ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ዕቅድ | በወቅቱ የተዘጋጀ ዕቅድ | 100% | 100% | - | | |
| | | | ከዕቅድና ከአፈጻጸም ክትትል አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሻሻል፤ | የባንኩን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማቀናጀት | በወቅቱ ዕቅድ ማዘጋጀት (በቁጥር) | 1 | 1 | - | - | - | |
| | | | | የባንኩን የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ማዘጋጀት | በወቅቱ ዕቅድ ማዘጋጀት (በቁጥር) | 1 | - | - | - | 1 | |
| | | | | የባንኩን የ2014 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት የዘጠኝ ወራት እና ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት | በወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀት (በቁጥር) | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | | የዕቅድ እና ክትትል የአሠራር መመሪያ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ መመሪያ (በቁጥር) | 1 | 1 | - | - | - | |
| | | | ከባንኩ የሥራ አፈፃፀም ምዘና አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ | የ2013 የባንኩ የውስጥና የውጭ የባለድርሻ አካላት እርካታ የዳሰሳ የጥናት ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የጥናት ሰነድ በቁጥር | 2 | 1 | - | 1 | - | |
| | | | | የባንኩ ሠራተኞች አፈጻጸም ግምገማ ውጤት ትንተና ሪፖርት ተዘጋጅቷል | በወቅቱ የተዘጋጀ ሪፖርት | 2 | - | 1 | - | 1 | |
| | | | ከኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት አንፃር የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ | የብሪቱ መጽሔትን በማሳተም ማሰራጨት | በወቅቱ የተሰራጨ የብሪቱ መጽሔት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | ለሚዲያ አካላት፣ ለጥናት አድራጊ ግለሰቦችና ባለጉዳዮች ተገቢዉን መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ | ለሚዲያ አካላት የተሰጠ መረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | | ለጥናት አድራጊ ግለሰቦች የተሰጠ መረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | | ለባለጉዳዮች በመረጃ ዴስክ በኩል የተሰጠ መረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የሚዲያ ዉጤቶች የዳሰሳ መረጃዎችን በመለየት ለባንኩ ከፍተኛ አመራር ማቅረብ | በወቅቱ እና በአግባቡ የተሰጠ መረጃ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | ቀልጣፋ የቅሬታ አፈታት አገልግሎት በመስጠት አንፃር የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ | ቅሬታ የማስተናገድ ሪፖርት | በወቅቱ የተዘጋጀ ሪፖርት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | | | ከኩነት ማኔጅመንትና ፕሮቶኮል አገልግሎት አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ | የፕሮቶኮል ሥራዎችን ማካሄድ፤ | በወቅቱ የተሰጠ አገልግሎት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | ከሴቶችና ወጣቶች አፈፃፀም አኳያ የባለድርሻ አካላትን እርካታማሳደግ | በባንኩ የህፃናት ማቆያ ለመመሥረት ክትትል ማድረግ እና ማጽደቅ | የጸደቀ መመሪያና ክትትል | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 100% | - | - | - | |
| | | | የባንኩን ሴት ሠራተኞች የምክር አገልግሎት መስጠትና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት | የተሰጠ የምክር አገልግሎት | በወቅቱ የተሠጠ የምክር አገልግሎት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | አለም አቀፍ የHIV/AIDS ቀን እና ነጭ የሪባን ቀንን በተለያዩ ትምህርታዊ ዝግጅቶች ማክበር | የተዘጋጀ የHIV/AIDS እና ነጭ የሪባን ቀን | የተዘጋጁ ኩነቶች በመቶኛ | 100% | - | 100% | - | - | |
| | | | አለማቀፍ የሴቶች ቀን በዓልን በባንኩ እንዲከበር ማስተባበርና መዘጋጀት | የተዘጋጀ የሴቶች ቀን | የተዘጋጁ ኩነቶች በመቶኛ | 100% | - | - | 100% | - | |
| | | | በባንኩ የፆታ ድጋፍ /affirmative action/ አፈፃፀምን መከታተልና ሪፖርት ማቅረብ | የፆታ ድጋፍ /affirmative action/ ክትትል | የፆታ ድጋፍ /affirmative action/ አፈፃፀም ሪፖርት (በቁጥር) | 1 | - | 1 | - | - | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| | 3.14 | | የኦዲትና የማማከር አገልግሎት ቅልጥፍናና ውጤታማነት ማሻሻል | ሪስክን (ስጋትን) መሠረት ያደረገ ኦዲት ማከናወን | የኦዲት ሪፖርት ብዛት | 10 | 3 | 3 | 2 | 2 | |
| | | | | የሪስክ ማነጅመንት ሪፖርት ማቅረብ | የቀረበ ሪፖርት ብዛት | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | | | | የዓመት እና የግማሽ ዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት | የተጠቃለለ ሪፖርት ብዛት | 2 | 1 | - | 1 | - | |
| | | | | በአሮጌ ብሮች የናሙና ቆጠራና የማስወገድ ሥራ እንዲሁም የውጭ ሀገር ገንዘብና ወርቅ ወደ ውጭ ሀገር ሲላክ በመገኘት የማረጋገጥ ሥራ መሥራት | ዕለታዊ ገለልተኛ የማረጋገጫ ሪፖርት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | 3.15 | | የባንኩን ጥቅም ማስከበርና በቂ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩን ማረጋገጥ | ክትትል የተደረገባቸው የፍትሕ ብሔርና የወንጀል ጉዳዮች | ሪፖርቶች | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | የባንኩ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎችና ውሎች መከበራቸውን ማረጋገጥ | በተለያዩ ሠነዶች ላይ የሕግ አስተያየትና ምክረ-ሐሳብ መስጠት፣ በመሻሻል ላይ የሚገኘውን የባንኩን ማቋቋሚያ አዋጅ ማጠናቀቅ፣ የኮሮና ወረርሽኝ ቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለተለያዩ የሥራ ክፍሎች ገለፃ (briefing session) ማዘጋጀትና ማቅረብ | የደንበኞች እርካታ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |

| እይታ | ተ.ቁ | የተቋሙ ዓመታዊ ስትራቴጂክ ግብ | የሥራ ሂደት ግብ | የሚጠበቅ ውጤት | ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የዓመቱ ዒላማ | የ2014 ሩብ ዓመታዊ ዒላማ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| 4. መማማርና ዕድገት | 4.1 | የሠራተኞችን የቴክኒክ ብቃት፣ አመራርና ባህል ማሻሻል | የሠራተኞችን የቴክኒክ ብቃት፣ አመራርና ባህል ማሻሻል | ተለይተው የታወቁና የተሞሉ የሙያ ክፍተቶችና የተሰጡ ሥልጠናዎች | አፈፃፀም በመቶኛ | 100% | 15% | 30% | 35% | 20% | |
| | | | | ሠራተኛውን ለማብቃት የተሠሩ ሥራዎች | የአፈፃፀም ክትትል | 100% | 25% | 50% | 75% | 100% | |
| | | | | የውጤት ተኮር ምዘና ክትትል፣ ግምገማና ግብረመልስ መስጠት | ወቅቱን የጠበቀ የውጤት ተኮር ምዘናና ክትትል | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | | | | የሠራተኞችን ባህርይ ከባንኩ ዋና ዋና እሴቶች ጋር ማዛመድ | የተደረገ ክትትል | 72% | 72% | 72% | 72% | 72% | |